# “ድርሳነ - ወሐቢያን” በወፍ በረር ዕይታ

## (ክፍል አንድ)

**አብዱልአዚዝ ከድር** - 7/20/12

አብዛኛው የጽሑፉ ክፍል “ተረት፣ ተረት - የመሰረት” እንዲሉት ዓይነት ነው፡፡ በመላ ምት የታጠረው ይህ ባለ 73 ገጽ ጽሑፍ፤ በ“ይሆናል፣ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ የሚከሰት ይመስለኛል፣ እንዲህ ሊደረግ ነው፣ ይህን ሊፈጽሙ ይችላሉ፣ የማይቀር ነው… ወዘተ” በሚሉ “የይሆናል ዓለም” ንግርት መሳይ ትርክቶች የታጨቀ ነው፡፡

ለምናባዊ የፈጠራ ድርሳንነት የተሰናዳውና ነባሩን እምነት “እሥልምና በማደጉ ምክንያት ተቀይሯል” በሚል ወልጋዳ አመክንዮ ለማጠልሸት የቀረበውን ይህ ጥራዝ፣ መንግሥት ላለፉት 21 ዓመታት የሀገራችንን ኃይማኖቶች ለማስፋፋት ያደረጋቸውን ጥረቶች ፈጽሞ አያውቀውም፤ ሊያውቀውም አይፈልግም፡፡

“በኢትዮጵያ እሥልምና ላይ የተቃጣው የኢህአዴግ ዘመቻ፣ መንስዔዎቹ፣ ተፅዕኖዎቹና ቀጣይ ሁኔታዎች” በሚል ርዕሰ ይህን የጥላቻ ዲስኩር ከመሰንበቻው በጽሑፍ መልክ ያነበነቡት አብደላህ አደም ተኪ የተባሉ የድርሳኑ ቀማሪ ግለሰብ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ጽሑፉ በእኚህ ግለሰብ ቢቀርብም ቅሉ፤ በውስጡ ያካተታቸው ጥንቆላዊ ይዘቶች በአሁኑ ወቅት የወሐቢያን አስተሳሰብ የሚያራግቡ ጥቂት ወገኖች “በመንግሥታዊ ሥርዓቱ ውስጥ ሙስሊሞች የሉበትም” በማለት የሚያቀነቅኑትን እሳቤ የያዘ በመሆኑ “ድርሳነ - ወሐቢያ” የሚል ሥያሜ ቢሰጠው የሚበዛበት አይመስለኝም፡፡

ይህ የመንግሥትና የኃይማኖትን መለያየት በይፋ ላለመቀበል የሚዳዳው ጽሑፍ፤ በውስጡ በርካታ የወሐቢያ ድርሣኖችንና “የቢሆን” ተስፋዎችን እንዲሁም በኢህአዴግ/በመንግሥት ላይ የጥላቻ አሉባልታዎችን ብሎም በኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ግራ የተጋቡ ትንታኔዎችን የያዘ ነው፡፡

እነዚህን “የሊሆን ይችላል ንግርቶች” አንድ በአንድ ዘርዝሮ ማቅረብ ረብ የለሽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ክፍል የጽሑፉን የመጀመሪያ 20 ገጾች በወፍ በረር ዕይታ በመቃኘት ለውድ አንባቢዎቼ እውነታውን በጠራና ትክክለኛ በሆነ ሁኔታ ለማመላከት እሞክራለሁ፡፡

በ“ድርሣነ - ወሐቢያ” ጽሑፍ ላይ ተደጋግመው ከተለገጹት ሰነዶች ውስጥ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ አንዱ ነው፡፡ “ሰይጣን ላመሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል” እንዲሉ አበው፡፡ ታዲያ ግለሰቡ በሰነዱ ላይ የጥላቻ በትራቸውን የመዘዙት “መንግሥት የሚያሰናዳቸው ፖሊሲዎች እሥልምናን ለማፈን የታለሙ ናቸው” በሚል እጅግ አስገራሚ “የአራምባና ቆቦ” ትንተና ነው፡፡

በዚህም የሀገራችን ተደማጭነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያድግና ከውጭው ዓለም ጋር አሁን ላለን መልካም ግንኙነት ወሣኝ ድርሻ በማበርከት ላይ የሚገኘውን ሰነድ ቃላቶችን እየመዘዙ እንዲሁም የራሳቸውን ጨለምተኛ እሳቤ እየጨመሩ በማብጠልጠል እንደ ማጣቀሻ ሊጠቀሙበት ለተመለከተ ሰው፤ ሰውዬው የሚከተሉት የወሐቢያ እምነት ፖለቲካዊ እንጂ ኃይማኖታዊ አለመሆኑን ለመገንዘብ አይከብደውም፡ ፡

በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ መንግሥት እርሳቸው እንዳሉት እሥልምናን የሚያፍን ፖሊሲ ሊቀርጽ ቀርቶ፤ ሀገራችን እሥልምናን ከማንም ሀገር፣ እንዲያውም ኃይማኖቱ ከመነጨበት ሣውዲ ዐረቢያ ጭምር ቀድማ ያስተናገደች ሀገር መሆኗን በሰነዱ ላይ ይፋ አድርጓል፡፡

በዚህም እሥልምና የብዙ ኢትዮጵያዊያን እምነት ብቻ ሳይሆን የታሪካችንና የባህላችን አንድ አካል መሆኑን በግልጽ አመላክቷል፡፡ የወሐቢያው ድርሳን ባለቤት የሆኑት ግለሰብ ግን ይህን ትክክለኛውን የሰነዱን እውነታ ከማየት ይልቅ፤ ከየት እንዳመጡት በማይታወቅ ሁኔታ ያልተጻፈን ልቦለድ ለማቀንቀን መሻታቸው አንዳችም ጠብ የሚል ሃቅ የሌላቸው መሆኑን የሚያመላክተን ነው፡፡

አቶ አብደላህ ፖሊሲው ላይ ያልሰፈረውን አሊያም ፖሊሲው ለማመላከት ያልፈለገውን ጉዳይ በራሳቸው “የአቦ - ሰጥ” ትንታኔ እየታገዙ በመዘላበድ ረገድ ወደር አላገኘሁላቸሁም፡፡ እርግጥ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው የእሥልምና እምነት እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ፤ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) “ሃበሻ ካልነካችሁ እንዳትነኩት” የሚል መልዕክት ማስተላለፋቸውንና ይህም ለኢትዮጵያ ያላቸውን ከበሬታ እንደሚያሳይ አውስቷል፡፡

የወሐቢያ ድርሳን ቀማሪው “መንግሥት ፖሊሲዬ ብሎ በያዘው አቋም ነጃሺ ሰልሚል የሚለውን አስተሳሰብ የሚያንቀፀባርቁ በሙሉ አክራሪዎች ናቸው ብሎ ፈርጇል” በማለት ያልተጻፈን ጉዳይ ከአዕምሮአቸው በማፍለቅ ለመሟገት ዳድቷቸዋል፡፡ በመሰረቱ ፖሊሲው ግልጽ ያደረገው ጉዳይ ቢኖር፤ ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር የነበራትን ግንኙነት ካሻከሩት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የኃይማኖት አክራሪነት መሆኑን እንደ ፖሊሲ ነገሩን ከስር መሰረቱ ማውሳት ብቻ ነው፡፡

በእነዚያ ጊዜያት አክራሪነት ሲጠናከር የኢትዮጵያ ለጥቃት ተጋላጭነት ይጨምር እንደነበር እንዲሁም ለዘብተኝነት ሲጠናከር ደግሞ የሀገራችን ግንኙነት ሲሻሻል መኖሩ አይታበይም፡፡ እርግጥም ዛሬም ድረስ አክራሪነት የኢትዮጵያ ሥጋት ሆኖ መዝለቁ ከማንም የሚሰወር ጉዳይ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ለግለሰቡ አሊያም ጽሑፉን በሰነድነት ላሰናዱት ወሐቢያውያን የሚዋጥላቸው ባይሆንም፡፡

የጽሑፉ አዘጋጅ በግላጭና በተዘዋዋሪ ለዘብተኝነትን በማውገዝ አክራሪነት መኖር እንዳለበት ለማሳሳብ ቢሞክሩም፤ የኃይማኖት አክራሪነት መቋጫው የሌላውን ኅብረተሰብ ክፍል እምነት በመድፈቅ፣ ‘እኔን ብቻ ተከተለኝ’ የሚል ኢ-ዴሞክራሲያዊ ቀኖና መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ግና ያለ አክራሪነት ኃይማኖትን ማራመድ የማይቻል የሚመስላቸው እንደ አቶ አብደላህ ዓይነት “ወሐቢያዊ ነብዮች” ይህን መሰሉን የሌሎችን መብት ረጋጭ ቀኖና ለማራገብ የሚሹ በመሆናቸው ፖሊሲውን አጣመው ቢተረጉሙ የሚገርም

አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ዋነኛ ዓላማቸው የመንግሥት ሰነዶችን በመጥቀስ ፖለቲካዊ አጀንዳቸውን ለማሳካት መቋመጥ እንጂ ኃይማኖታዊ ስላልሆነ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ እስቲ ወደ "ወሐቢያው ሰነድ" እናቅና፡፡ ሰነዱ ራሱን በራሱ የሚከላከል ነው፡፡ "ወሐቢያ የጥፋት አንጃ ከሆነና በየቦታው ካለ፣ በኢህአዴግ ዘመን እምልምና የተሰፋፋው የት ይሆን?" የሚል ጥያቄና ሌሎች እንካ - ሰላንቲያዎችን በማቅረብ፡፡ እርግጥ ግለሰቡ እንዳሉት ወሐቢያ ዜጎችን በማስገደድ 'የእኔን እምነት ብቻ ተከተል' የሚል በመሆኑ፣ በሀገራችን ስር በመስደድ ላይ ለሚገኘው ዴሞክራሲ እንቅፋት በመሆኑ የጥፋት አንጃ ነው፡፡

ሆኖም የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች እርሳቸውና ጥቂት መሰሎቻቸው እንጂ አብዛኛው ሙስሊም አይደለም፡፡ እነዚህ ወገኖች ምናልባትም የራሳቸው ፍላጎት ባላቸው የውጭ ኃይሎች የገንዘብ ድጋፍ እየታገዙ በየቦታው ለጥፋት ተልዕኳቸው ቢዘሩም፣ ሁሉም ቦታ የሚገኙ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡

አብዛኛው የእምነቱ ተከታይ በየቀኑ በአክራሪው ቡድን ላይ የሚያሰማው ተቃውሞ ፖለቲካዊ አጀንዳ ያነገበውን ወሐቢያን እንደማይቀበለው እንጂ ደግፎት አይደለም፡፡ እናም ጽሑፉ እንደተመኘው ሳይሆን የጽንፈኝነት አስተሳሰብን የሚያራምደው ቡድን በብዙኃኑ የተተፋ መሆኑን ሰሞኑን የሚካሄዱ የ"ዞር በሉልን" ጥያቄዎች አፋቸውን አውጥተው የሚናገሩ ለመሆናቸው መስካሪ የሚያሻቸው አይመስለኝም፡፡

የሰነዱ አስቂኝ ጥያቄ "… በኢህአዴግ ዘመን እምልምና የተስፋፋው የት ይሆን?" የሚለው ነው፡፡ እርግጥ ይህን አስገራሚ ጥያቄ ሀገራችን ውስጥ ላለፉት 21 ዓመታት የኖረ የእምነቱ ተከታይ ያቀርባል ብሎ መናገር ያስቸግራል - ወሐቢያ ከተስፋፋባቸው የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የመጣ አሊያም በእነርሱ ገንዘብ የታወረ ካልሆነ በስተቀር፡፡

ማንኛውም የሀገራችን ሙስሊም እንደሚገነዘበው፣ ከደርግ ውድቀት በኋላ ሀገራችን ውስጥ የኃይማኖት እኩልነትና የእምነት ነጻነት ህገ - መንግሥታዊ ዋስትና አግኝተዋል፡፡ ቀደምት ሥርዓቶች ይከተሉት በነበረው የኃይማኖት ጭቆና መርህ ምክንያት የተፈጠሩና ስር ሰደው የነበሩ የፍትህ መጓደሎች ታርመዋል፡፡ እምልምናን ጨምሮ የሌሎች ኃይማኖቶች ማምለኪያ ቦታዎች እንዲስፋፉ ተደርገዋል፡፡ ሌላው ቢቀር ላለፉት ሁለት አሥርታት የት የለሌ መስጂዶች እንደተሰሩ እንዲሁም በዓፄውና በደርግ ሥርዓቶች የማይታወቁት ኃይማኖታዊ በዓላቶች እውቅና በማግኘታቸው ከህዝብ ሙስሊሙ ህሊና የሚሰወር ጉዳይ አይደለም፡፡

ታዲያ "የወሐቢያው ሰነድ" የሚዘላብደው ምንድነው? ገዥው ፓርቲ እንደ መንግሥት ኃይማኖት የሚስፋፋበትን መደላድል ስላልፈጠረ፣ እኔ ነኝ የማስፋፋላችሁ እያለን ይሆን እንዴ? እርግጥም ሃሳቡ ይህ ከሆነ 'ዓላማዬ  መንግሥት መሆን ነው' የሚል ግልፅ አንድምታ ስላለው በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ መስፈርት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ለምን ቢባል፣ ሀገራችን ውስጥ ማንኛውም ቡድን በመንግሥትነት ሀገርን ሊያስተዳድር የሚችለው በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንጂ፣ የኅብረተሰቡን ሠላማዊ ህይወት በሚያውክ

የሁከት ፈጠራ ተግባር ስላልሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሠላምና ከዴሞክራሲ እሳቤዎች ጋር ጠበኛ ለሆኑት የድርሳኑ አቀንቃኞች የሚቻል አይደለም፡፡

ሰነዱ ራሱን በራሱ ለመከላከል ሲልም መገለጫዎቹን መልሶ ተሳልቆባቸዋል፡፡ ይኸውም "ወሐቢያ ለአስተሳሰብ ልዩነት ክብደት አይሰጥም፣ ቀደምት ሀገር በቀል ሼኮችን አምርረው ይጠላሉ፣ እንዲገለሉ ያደርጋሉ… ቀደምት መስጊዶችን ታሪካዊ ቦታዎችንና ገዳማትን ለማቃጠል ይሞክራሉ፣ በቻሉት ቦታ ሁሉ ኃይል ይጠቀማሉ…ወዘተ. እንባላለን" በሚል የአዞ እንባ ማንነቱን ለመካድ ሞክሯል፡፡ በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት ግን፤ እነዚህ ተግባራት የአክራሪው ወሐቢያ መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ ለዚህም በርካታ አስረጅ እውነታዎችን መዘርዘር ይቻላል፡፡

ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው ጽንፈኛው ቡድን ለአስተሳሰብ ልዩነት ክብደት አይሰጥም እንደተባለው ሳይሆን፤ ከእነ አካቴው የአመለካከት ልዩነቶችን አይቀበልም፡፡ ሁሌም ቢሆን 'እኛ ያልነው ትክክል ነው' ባይ ነው፡፡ ለአንድ የወሐቢያ እምነት ተከታይ ከእርሱና የእርሱን ፈለግ ከሚከተሉ ወገኖች ውጭ ሌላው ኃይማኖተኛ ትክክል አይደለም፡፡ ቡድኑ ከመቻቻል ይልቅ መናቆርን፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከሠላም ይልቅ ሁከትን የሚናፍቅ ለመሆኑ ከመሰንበቻው በአወሊያ እና በአንዳንድ መስጊዶች ያካሄዳቸው የነውጥ ተግባራት ተጠቃሽ የማንነቱ መገለጫዎች ናቸው፡፡

እርግጥም የቡድኑ አባላት ቀደምት ሀገር በቀል ሼኮችን አምርረው የሚጠሉ፣ እንዲገለሉም የሚሹ ናቸው፡፡ ሰሞኑን ነባሮቹን የእሥልምና  አባቶች በማውገዝ፣ መጅሊስ አይወክለንም ማለታቸው የዚህ ማንነታቸው ነፀብራቅ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች በመቻቻል ባህላችን ላይ ጦር የሰበቁ በመሆናቸው፤ ከሌላው ኃይማኖት ጋር በሠላምና በፍቅር መኖር እንደሚገባ የሚያስተምሩ ሼኮችንና ኡስታዞችን ከማጥላላት አልፈው በምርጫ ወቅት እንዳይሳተፉ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ እያካሄዱ ነው፡፡

የዚህ ሁሉ ተግባራቸው ድምር ውጤት እነዚህ ወገኖች ኃይማኖትን የፖለቲካ መነገጃ ለማድረግ ያላቸውን ውስጣዊ ቀቢፀ - ተስፋ የሚያመላክት መሆኑ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም፡፡ ራስን ብቻ በማዳመጥ ለዘመናት ህዝቡን ሲያስተምሩ የኖሩ ኃይማኖቶችን  የማውገዝና እንዲገለሉ የማድረግ መሰሪ አባዜ፡፡

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት "ድርሳነ - ወሐቢያ"  በገደምዳሜው የማንነቱ መገለጫ አይደለም ለማለት የሞከረውና ቀደምት መስጊዶችን፣ ታሪካዊ ቦታዎችንና ገዳማትን  ማቃጠልና ለማቃጠል የመሻት ፍላጎት እውነተኛ ዓላማው ነው።

ምክንያቱም ይህ ተግባር የማንኛውም ኃይማኖታዊ አክራሪ ቡድን መገለጫ ከመሆን በዘለለ የህልውናው መሠረት ጭምር በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ጥቂት አብነቶችን ማንሳት እችላለሁ፡፡

ከዛሬ አራትና አምስት ዓመታት በፊት በኦነግ ወይም ኦነግ በነበሩ ሰዎች አማካይነት "ሃዋርጅያ" በተባለ የሙስሊም አክራሪዎች ቡድን በምዕራቡ የሀገራችን ክፍል የተፈፀመውን አሳዛኝ ታሪክ ሁላችንም እናስታውሳለን፡፡ በወቅቱ እነዚህ ወገኖች በብሔር መብት ዙሪያ ያካሂዱት የነበረው እንቅስቃሴን ሚዛናዊው

የሀገራችን ህዝብ "ነጻ ወጥቻለሁ፣ ሌላ ነጻ አውጪ አያስፈልገኝም" በማለቱ ተቀባይነት ሲያጡ፤ የጥፋት ማርሻቸውን ወደ ኃይማኖት በመቀየር በምዕራቡ ክፍል የሚገኙ በርካታ ዜጎች ለህልፈተ - ህይወት እንዲዳረጉ፣ ቤት ንብረታቸው እንዲወድም እንዲሁም ነባር መስጊዶችንና ቤተ - ክርስቲያኖችን ማቃጠላቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡

ምንም እንኳን ይህን መሰሉ በኃይማኖት ሽፋን የሚደረግ የፖለቲካ ሩጫ የማታ ማታ ህዝቡ ለሠላም ባለው ቀናዒ ፍላጎት መክሸፉ የማይቀር ቢሆንም፤ የአክራሪነት ድርጊቱ ግን ነባር ሀገራዊ ቅርሶችን በማፈራረስና በማውደም ላይ የሚያጠነጥን መሆኑን በገሃድ አመላክቶን አልፏል፡፡

ሁኔታውን ከአፍሪካዊ ክስተቶች አኳያ ስንመለከተው ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ሰሞኑን የማሊ እሥልምና አክራሪዎች በሰሜናዊ ማሊ "ቲምቡኩቱ" በተሰኘች ከተማ ውስጥ የሀገሪቱን ነባር ቅርሶች በመጥረቢያ ሲያወድሙ በመገናኛ ብዙኃን መመልከታችን፤ በጽንፈኝነት የተነሳ ማንኛውም ቡድን "የእምነት ጉዳይ ከእኔ ወዲያ ላሳር" የሚል መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

ይህም እንደ ወሐቢያ ዓይነት አክራሪዎች ነባር ሀገራዊ ሀብቶችን ማውደም ቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ምናልባትም ልክ እንደ ማሊው የእኛዎቹ ፅንፈኞችም ነገ እንደ ድሬ ሼክ ሁሴን ዓይነትንና ሌሎች መሰል ሀገራዊ ቅርሶችን ላለማውደማቸው ማን እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? - ማንም፡፡

"ድርሳነ - ወሐቢያ" በራሱ መገለጫ ላይ የተሳለቀበት ሌላኛው ነጥብ፣ ወሐቢያ ሁከት ፈጥሮ ኃይል እንደማይጠቀምና በድንጋይ ሰው ወግሮ እንደማይገድል በማስመሰል ለማስተላለፍ የፈለገው አስገራሚ አባባል ነው፡፡ ግና ነገሩ "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንዲሉት ዓይነት መሆኑ ከዚህ ጽሑፍ አንባቢ የተሰወረ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በመገናኛ ብዙኃን እንደተመለከትነው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተሰማሩት እፍኝ የማይሞሉ የፅንፈኛ የቡድኑ ተከታዮች በሌላው ዓለም ክቡር በሆነው የህዝብ ሠላም ጠባቂ ፖሊስ ላይ ድንጋይን እንደ በረዶ ሲያዘንቡ ነበር፡፡

ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ውስጥም አንድ መስጊድ ውስጥ የሚያገለግሉ ሼክን የቡድኑ አባላት ደብድበው ገደል ውስጥ እንደከተቷቸው መገናኛ ብዙኃን ይፋ አድርገዋል። እነዚህ ሀቆችም ራሱን "ወሐቢያ" እያለ የሚጠራው አክራሪ ቡድን፤ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ፖሊስን ሳይቀር መደብደብ እንዲሁም ማንኛውንም ከእነርሱ ፍላጎት በተፃራሪ የቆመን ግለሰብ ማስወገድ የተግባር መመሪያው እንደሆነ በይፋ ያረጋገጠበት ክስተቶች ነው፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ 'የድርሳኑ ፀሐፊም ይሁን አስጻፊያቸው ቡድን ስለምን በራሳቸው ማንነት ላይ ይሳለቃሉ?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ እውነታው ግን እንዲህ የሚነበብ ነው፡፡ … እንደሚታወቀው ማንኛውም ኃይማኖትን በግርዶሽነት የሚጠቀም ፖለቲካዊ ኃይል ኃይማኖታዊ ጥያቄዎች ስለሌሉት፣ ያለው አማራጭ ራሱን ለመደበቅ እምነቱን ማራከስ ብቻ ነው፡፡ እንቅስቃሴውም ኃይማኖታዊ ባለመሆኑ የሚፈፅማቸው ተግባራት ከኃይማኖቱ አስተምህሮቶች አኳያ ስለሚመዘኑ እውነተኛ ማንነቱን ለመደበቅ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" ስልትን ይከተላል፡፡ "ድርሳነ ወሐቢያም" ሆኑ ፀሐፊው ያደረጉት

ይህንኑ ነው፡፡ ማጣፊያው ሲያጥርባቸው ዓይናቸውን በጨው ታጥበው በራስ ላይ በመሳለቅ ራስን ለማታለል መሞከር፡፡

የወሐቢያው አቀንቃኝ አሊያም አስቃንቃኞቻቸው ከህገ - መንግሥቱ ጋር በገሃድ የተጋጩ መሆናቸውንም በሰነዳቸው ላይ አውስተዋል፡፡ እናም በሚያስገርም ሁኔታ "በትምህርት ቦታዎች መስጊድ እንዲሰራ፣ በትምህርት ሰዓት ሰግደት እንዲፈቀድ መጠየቅ  መብት እንጂ አክራሪነት ነውን?' በማለት ይጠይቃሉ፡፡

እንግዲህ ውድ አንባቢዎቼ እዚህ ላይ ልብ ይሏል!  የሰነዱ ፍላጎት ምን እንደሆነ፡፡ እርግጥም "ድርሳነ - ወሐቢያ" መንግሥትና ኃይማኖት እንዲሁም መንግሥታዊ የትምህርት ተቋማትና ኃይማኖት የተለያዩበትን ህገ - መንግሥታዊ ድንጋጌ ፈፅሞ እንደማይቀበለው እየነገረን ነው፡፡

አዎ! ይህ ወሐቢያዊ ውግኔ ቀደም ሲልም ይታወቃል፡፡ ልዩነቱ ባለፉት ጊዜያት እሳቤውን ውስጥ ለውስጥ የሚያከናውነው ሲሆን ዛሬ ላይ ግን በተግባሪዎቹ ሰነድ በይፋ መገለጹ ብቻ ነው፡፡ ለመሆኑ በትምህርት ቦታዎች ላይ መስጊድ  እንዲሰራና በትምህርት ሰዓት ስግደት እንዲከናወን መጠየቅ 'ኃይማኖትንና የመንግሥት ሥራዎችን በአንድ ላይ አቀራኝተን እንፈጽም' ማለት መሆኑን እነዚህ ወገኖች ይረዱት ይሆን? እንዴታ፣ በሚገባ ነዋ፡፡ ታዲያ ይህ ማለት መንግሥታዊ ኃይማኖት ይኑር ከሚለው የቅዥት ዓለም ቀኖናቸው የተለየ እንዳይመስላችሁ፡፡

ይሁን እንጂ ኃይማኖትን ከመንግሥታዊ ሥራዎች ጋር መሳ ለመሳ አደባልቆ ማስኬድ ኃይማኖት በመንግሥት፣ መንግሥትም በኃይማኖት ውስጥ ገብተው "ይህን አድርግ፣ ያኛውን ደግሞ አታድርግ" እንዲሉ የተመቻቸ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ግና እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ከዓጼውና ከደርግ ሥርዓቶች ጋር ግብዓተ - መሬቱ ተፈጽሟል፡፡

ዛሬ ግን ምሥጋና ለኢፌዴሪ ህገ - መንግሥትና እርሱን እውን ለማድረግ የማይተካ ህይወታቸውን ቤዛ ላደረጉ ውድ የሕዝብ ልጆች ይግባቸውና፤ የተወሰኑ ዜጎች ኃይማኖታዊ እምነት በሌሎች ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በኃይል የሚጫንበት ዕድል ሙሉ ለሙሉ መዘጋቱን የድርሳኑ አቀናባሪዎች ሊረዱት ይገባል፡፡

በመሆኑም የማንኛውም ኃይማኖት እኩልነትና የእምነት ነጻነት መታየት ያለበት ከህገ - መንግሥቱ ካነናጸፈን መሠረታዊ መብቶች አኳያ እንጂ፤ ከፅንፈኞች ፍላጎት አንጻር ሊሆን እንደማይችል በጄ ነው፡፡ በህገ - መንግሥቱ ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የወሐቢያ አስተምህሮ ተከታዮች በዚህ መልኩ የሚጻረሩት ከሆነ፤ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ህገ -መንግሥቱንና ህገ - መንግሥታዊ ሥርዓቱን ብሎም የሕዝቦችን የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ትሩፋቶችን ከማስጠበቅ አኳያ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ይመስለኛል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ "ድርሳነ - ወሐቢያ" በሚያስገርም ሁኔታ "የአብዬን ወደ እምዬ" እንዲሉት ዓይነት በሰነዱ ውስጥ "…መደበኛ ኢሥላማዊ እና ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሁነቶችን አሻራቸውን ለማጥፋት ነባሩ

እሥልምና (በእነርሱ አጠራር አህባሽ) እየተንቀሳቀሰ ነው”  በማለት ያዘነበውን የአዞ እንባ እና ሌሎች የድርሳኑን አስቂኝ ትንቢያዎችን በቀጣዩ የጽሑፌ ክፍል የምዳስስላችሁ ይሆናል፡፡ እስከዚያው አላህ ቸር ያሰንብተን፡፡